Date 05/06/2023

ይድረስ ለJimma University President Dr. Jemal Abafita

እኛ የJimma University ተማሪዎች አሁን ያለንበት ሁኔታ ከአቅም በላይ በመሆኑ ይሄን ሁኔታ ታሳቢ እንዲደረግልን እንጠይቃለን::

ቀደም ብሎ ተነግሮን የነበረው የጊዜ ለአንድ ሰሚስተር 45 ተይዞ መማር ጀምረን ቢሆንም አሁን ያለን ጊዜ ከ 45 ወደ 30 ቀን መቀየሩን ብዙ አስተማሪዎቻችን እየነገሩን ነው ይሄ ደግሞ በፍፁም ማይሆን እና የግቢውን አላማ ሚያቃርን ነው. ቀደም ባለው schedule 120 ቀን ለ አንድ ሰሚስተር ሚሰጥ የነበረው ወደ 45 ይባስ ብሎ ደሞ አሁን ወደ 30 ቀን መውረዱ አደገኛ ዉሳኔ በመሆኑ ይሄ ዉሳኔ ድጋሚ እንዲታይ እንጠይቃለን, ካልሆነም አሁን ግዴታ በ30 ቀን ማለቅ አለበት ከተባለ ለምን ;

1, ምኖስዳቸዉ የcourse ብዛት እንዲቀነስ አልተደረገም (ለምሳሌ ከ 7 course በላይ ለሚወስዱት ተማሪዎች)

2, አሁን በዚ ፍጥነት ምንማረዉ ትምህርት እንዴት ለexit exam ሊያግዘን ይቻላል ወይስ ምን ታስቦ ነው?

3. በተለይ ለ3ኛ ዓመት ተማሪዎች አሁን ያሉበት ሁኔታ በሥርዓት ፕሮጀክት መስራት በነበረባቸው ሰዓት እንዲ ጊዜው በማጠሩ ብዙ ማወቅ ያለባቸውን እዉቀት ሳያቁ ሊያልፉ ስለሆነ ይሄ ደሞ የትምህርትን ጥራት ከማስጠበቅ አንፃር ምን የታሰበ ነገር አለ?

4. በዚ አካሄድ ከተሄደ በተማሪዎች ላይ ሊያጋጥም ሚችለው ዉድቀጥ ግቢዉንስ ተጠያቂ አያረገዉም ወይ?

እኛም ትውልድ በመሆናችን ለ 12ኛ ክፍል ፈተና እና Exit Exam ተብሎ እኛም መጎዳት ስለምንችል በተባለው ጊዜ አስከ MidExam ተምረን እና ቀጣይ ስንመጣ ፕሮጀክት እና Final Exam እንድንፈተን ወይም መፍትሄ ሚሆን ነገር እንድትሰጡን በአክብሮት እንጠይቃለን!

ከሰላምታ ጋር